# ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ

# Coalition for Unity and Democracy Party (Kinijit)

http://www.kinijitethiopia.org
e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974


ኪል-014/07
ግንቦት 7 ቀን 1999 ዓ.ም
May 15 , 2007

**የግንቦት 7 1997 ምርጫን በመዘከር ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ::**

## ግንቦት 7 1997 የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲያዊ መብቶቹ መከበር ያለውን ተቆርቋሪነት ያረጋገጠበትና የአምባገነንነት ፍጻሜ መቃረቡን ያበሰረበት እለት ነው::

ግንቦት 7 1997ን ቅንጅት እንደ ፖለቲካ ድርጅት ሲያስታውስ ከሁሉም ነጥቦች በላይ አልቆ ከሚያየው ከአንድ መሰረታዊ ቁም ነገር ጋር በማስተሳሰር ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ በግል፣ በማህበራዊ ህይወቱ፣ በሃገሩና ከእዚህ አልፎ በአካባቢው ጉዳይ ላይ፣ እድሉ ከተሰጠው የማሰላሰል፣ የመምከር፣ የመወሰን ብስለትና ብቃት ያለው ህዝብ መሆኑን ነው:: ድህነቱ ማይምነቱ የመከራ ህይወቱ እንደ ነጻ ህዝብ የማሰብ፣ የመወሰን ሰብአዊ ተሰጥዎውን ያልገፈፈው፣ እንዲያውም ነጻነቱን በከፍተኛ መስዋእትነት ተከላክሎ በማስጠበቁ፣ ለሃገሩ ነጻነት ብቻ ሳይሆን በግል ሕይወቱ ጭምር ሊኖር ሰለሚገባው ነጻነት ከፍተኛ ቀናኢነት የሚሰማው ኩሩና ድንቅ ህዝብ መሆኑን ነው::

ግንቦት 1997 የኢትየጵያ ህዝብ የሚገኝበትን የድህነት የመከራ ህይወት በማጣቀስ፣ ነጻነትና ዴሞክራሲ የማይገባው አድርገው ሲያዩት የነበሩትን የውጭ መንግስታት ኤክስፐርቶችና ምሁራን፣ በሃገራችንም «ህዘብ ለስልጣን ባለቤትነት የሚያበቃው ብስለት የለውም» በማለት የራሳቸውን አምባገነን አገዛዝ ለመጫን ሰበብ ሲያደርጉት የኖሩትን ገዥዎችና ገዥ ለመሆን ያኮበኮቡ ወንድሞቻቸውን ያሳፈረበት እለት ነው::

በግንቦት 97 ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ በጥላቻ ፖለቲካ ሳይሆን፣ የገዥው ፓርቲ ለአስራ አራት አመት በስራ ላይ ያዋላቸውን ፖሊሲዎችና በግንቦቱ የምርጫ ውድድርም በገዥው ፓርቲ ታላላቅ ባለስልጣናትና ካድሬዎቹ ተንትነው ያቀረቡለትን፣ ከእነዚሁ ፖሊሲዎች የሚመነጭ የወደፊት ራእያቸውን አዳምጦ፣ እነዚህንም ፖሊሲዎች ቅንጅት በአማራጭነት ካቀረባቸው የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ፣ የሃገር ደህንነትና ጥቅም ማስጠበቂያ ፖሊሲዎች ጋር በማነጻጸር ድምጹን መስጠት የቻለ ህዘብ ነው::

የግንቦቱ ታላቅ ድል የተለየና ታሪካዊ የሚያደርገው የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱን እጣ ፋንታ በራሱ መወሰን የሚችል የየትኛውንም ግለሰብ፣ ቡድን፣ ድርጅትና መንግስት ሞግዚታዊ ችሮታ የማይፈልግ መሆኑን ለአንዴና ለመጨረሻ ግዜ ያረጋገጠበት መሆኑ ነው:: የኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግር፣ ይህንንም ተከትሎ የሰፈነው ብልሹ አስተዳደር፣ የእዚህም ብልሹ አስተዳደር ውላጅ የሆኑት ረሃብ፣ በሽታ፣ ማይምነትና ሌሎችንም ነቀርሳዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመገንባት እድሉን ሲያገኝ ባጭር ግዜ ውስጥ የሚያስወግዳቸው ጉዳዮች እንደሆኑ በግልጽ የተንጸባረቀበት ድል ነው::

ግንቦት 97፣ ለህዝብ ክብር የሚሰጡ፤ በህዝባቸው የነጻነት ቀናኢነት፣ በሳልነትና አዋቂነት የማይጠራጠሩ፤ አይገባውም ብለው ሳይንቁት በየገጠሩና በየከተማው ጉራንጉር በመዘዋወር፣ በተወሳሰቡ ጉዳዮች ላይ ሊያማክሩት የሚፈልጉ መሪዎች ካገኘ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያኮራ ምላሽ መስጠት የሚችል ህዝብ መሆኑ የታየበት ወር ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ለማድረግ ለቻሉት እውነተኛ መሪዎቹ፣ ከግንቦት ምርጫ በፊት  በከተማና በገጠር በየስብሰባዎቹ በሽዎች በመገኘት፣ በማድመጥና በመምከር ብቻ ሳይሆን፣ ከእዚህ ምክክር በመነሳት በምርጫው ወቅት ለቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ በሰጠው ከፍተኛ ድምጽ አስመስክሮታል:: በኢትዮጵያ ውስጥ ህዘብን የሚያከብሩና ህዘብን ለማገልገል ቆርጠው የተነሱ የሃገሪቱ የፖለቲካ ምሁራንና የኢትዮጵያ ህዝብ ሲገናኙ፣ ህዝብ ተአምር መስራት የሚችል  መሆኑን ለአለም ያስመሰከረበት እለት ግንቦት 7 1997 ነው::

የእዚህ ተአምር ክፋይ የሆኑት የቅንጅት መሪዎች ዛሬ በወያኔ/ኢህአዴግ እስር ቤት በሃሰት ክስ ተወንጅለው መከራቸውን የሚያዩ መሆናቸው፣ ለመብቱና ለነጻነቱ በቆመው ህዝብ ላይ ወያኔ ያካሄደው ግድያ፣ እስራት፣ ማሳደድ፣ ማፈናቀልና አጠቃላይ እመቃ ግንቦት ፈንጥቆት በነበረው ተስፋ ላይ ጊዚያዊ ጥላውን ቢያጠላ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በግንቦት የተጎናጸፈውን ድል ሊሰርቀው አይችልም:: ይህ ድል የኢትዮጵያ ህዘብ በአምባገነንነት ላይ የተጎናጸፈው ሊፋቅ የማይችል ታሪካዊ ድል ነውና::

በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ይህንን ቀን ስናስታውስ ለሰለም፣ ለዴሞክራሲ፣ ለነጻነትና ለአንድነት የተሰውትን፣ በእስር የሚማቅቁትን፣ ቤተሰባቸውን በትነው የተሰደዱትና የተፈናቀሉትን እየዘከርን ብቻ ሳይሆን፣ የኢትዮጵያ ህዘብ በግንቦት 97 ምርጫ በፈጸመው ታላቅ ታሪካዊ ክንዋኔ በተስፋና በኩራት ተሞልተን ነው:: እንዲህ አይነቱን ቀን ስናስታውስ የግንቦትን ድል ሰንቀን በሃገራችን የፖለቲካና የሲቪል ነጻነቶች፣ የህግ የበላይነትና የስበአዊ መብቶች የሚከበሩበት፣ እኩልነትና አንድነት የሚነግሱበት፣ በድህነት ቦታ ብልጽግናን በኋለቀርነት ምትክ ዕድገትና ግስጋሴን የምናይበት ቀን ለማቃረብ የትግል ቃልኪዳናችንን የምናጠብቅበት አድርገን ነው::

በእስር የሚንገላቱት የቅንጅት መሪዎች ይህን ቀን ስናስብ በዋንኛነት የነሱን መንገላታት መአከል አድርገን ሳይሆን፣ በእዚያች የግንቦት ምርጫ እለት የኢትዮጵያ ህዝብ ከቅንጅት ጋር በመሆን በአምባገነንት ላይ የተቀዳጀውን ታላቅ ገድል በከፍተኛ ኩራት እንዲያስታውሰው፣ ይህንንም ድል በቀናኢነት እንዲንከባከበው እንደሚፈልጉና ይህንን ፍላጎታቸውንም ፍላጎታችን አድርገን ነው::

የግንቦት ድል በኢትዮጵያ የአምባገነንነት ማክተሚያ የመጀመሪያው ምእራፍ መዝጊያ እንጂ የመደምደመያው ምእራፍ መጨረሻ አለመሆኑን ሁላችንም ተገንዝበን፣ ለግንቦት ድል ያበቁንን መሰረታዊ ቁምነገሮች በመረዳት የቀጣዮቹ ድሎች መሰረቶች አድርገን መንቀሳቀስ ይገባናል::

የግንቦቱ ድል ለዴሞክራሲና ለነጻነት በጋራ በቆሙ ሃይሎች የተገኘ ድል ስለሆነ፣ ለእንዲህ አይነቱ አንድነት መመስረትና መጠናከር አምሮ በመስራት፣

የግንቦቱ ድል የግልጽነት፣ የተጠያቂነትና የአሳታፊነት ዴሞክራሲያዊ መርሆች በስራ ላይ በመዋላቸው የመጣ ድል በመሆኑ፣ ይህንን የዴሞክራሲ ባህል ይበልጥ እንዲዳበር በማድረግ፣

የግንቦቱ ድል እውቀትን ልምድን የጥናትንና የምርምርን አቅም አካቶ በተሰጠ አመራር ስር የተገኘ በመሆኑ በመጪው ትግላችን ለእነዚህ እሴቶች ታላቅ ቦታ በመስጠት፤

ከሁሉም በላይ፣ የግንቦት ድል ህዝብ በገዛ የህይወቱ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ብስለት አቅምና ብቃት አለው በሚል አመኔታ ላይ ቅንጅት የተሳተፈበት በመሆኑ፣ ለእዚህም የቅንጅት እምነት ትክክለኛነት በቂ ማስረጃ በመሆን የግንቦቱ ድል የሚያበራ በመሆኑ፣ በየትኛውም ቦታ ህዘብን የእንቅስቃሴያችን እምብርትና ባለቤት አድርገን ለመስራት ቃል በመግባት የምናሰታውሰው ሊሆን ይገባዋል::

ለግንቦት 7 የድል ቀን መሳካትና ይህንን ህዝባዊ ድል ከአምባገነኖች ጥቃት ለመከላከል መስዋእትነት የከፈሉትንና እየከፈሉ የሚገኙትን ወገኖቻችንን እያስታወሰን ሁላችንም የግንቦት ድል ያበሰረውን ጅማሮ ከግቡ ለማድረስ በጋራ አንነሳ።

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ